# ከገንዘብ ተቋማት ጋር በገጠምዎ ችግር እርዳታ ይፈልጋሉ?

## ስለ እነዚህ ሐብቶች የበለጠ ይወቁ።

ነዋሪዎች ከባንካቸው፣ ከኢንሹራንስ ድርጅታቸው፣ ከሞርጌጅ አበዳሪያቸው፣ ከኢንቨስትመንት አማካሪያቸው ወይም ከሌሎች የገንዘብ አገልግሎት ድርጅቶቻቸው ጋር ባለ ችግር እርዳታ እንዲያገኙ መጠየቅ ይችላሉ። እኛ— የዲሲ መንግስት— ችግርዎን በዝርዝር ከገመገምን በኋላ ችግርዎን ለመፍታት ስለሚኖረው መፍትሄ ከእርስዎ ጋር አብረን እንሰራለን። ጉዳዩ ተጨማሪ ምርመራ ወይም የወንጀል ክስ የሚጠይቅ ከሆነ፣ ጉዳዩን ወደሚመለከታቸው ባለስልጣናት እንልከዋለን።

ይህ አገልግሎት የተጠቃሚ ቅሬታዎች ይባላል እናም የቀረበው በኢንሹራንስ፣ ደህንነቶች እና ባንኪንግ ክፍል ነው።

## ብቁ መሆንዎን ያጣሩ።

ዲሲ ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ ብቁ ነዎት።

## እገዛ ይጠይቁ።

1. ከተቻለ፣ መጀመሪያ ችግር እንደገጠመዎ በማሳወቅ ከገንዘብ ተቋምዎ ጋር ይገናኙ።
2. የገንዘብ ተቋሙን በቀጥታ ለማግኘት ካልፈለጉ ወይም ችግርዎት ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ካልተስተናገደ፣ ከዲሲ መንግስት በአንላይን ወይምቅጽ ለ disbcomplaints@dc.gov ላይ ወይም 1050 First St. NE, Suite 801, Washington, DC 20002 ላይ በማስገባት እርዳታ ይጠይቁ። ችግርዎትን በዝርዝር ማስረዳት ይጠበቅብዎታል እንዲሁም ችግርዎትን ለመመዝገብ የደብዳቤዎችዎን ቅጂዎች፣ ደረሰኞች እንዲሁም ሌሎች ሰነዶችን ያጠቃልሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ይሰብስቡ።

## ካመለከትኩ በኋላ ምን ይሆናል?

1. እኛ — የዲሲ መንግስት— የእርስዎን ጥያቄ ባገኘ **በሶስት የስራ ቀን ውስጥ የማረጋገጫ ደብዳቤ በፖስታ በኩል እንልክልዎታለን**። ደብዳቤው ችግርዎትን የሚገመግመው ግለሰብን ስምን አጠቃልሎ ይይዛል።

2. የችግርዎን እውነታነት እንገመግማለን፣ የዲሲ ህጎችንና ደንቦችን እንተነትናለን እንዲሁም ተቋሙ ምላሽ እንዲሰጥ እናነጋግራለን።

3. ተቋሙ የዲሲ ህጎችና ደንቦች መጣሱን ካወቅን፣ ተቋሙ ችግሮቹን እንዲያስተካክል እንጠይቃለን። ይህ ካልሆን፣ ምንም እርምጃ አይወሰድም።

4. **በ 45 ቀናት ውስጥ** ጉዳዮን ለመጨረስ የቻልነውን ያህል እንሰራለን። ከምርመራው የመጨረሻ ሁኔታ ጋር አድርገን ለእርስዎ በፖስታ ደብዳቤ እንልክልዎታለን እና ማንኛውም ቀጣይ እርምጃዎች ካስፈለጉ ወቅታዊ መረጃን እንልካለን።

ጥያቄዎ በደረሰን በሶስት ቀናት ውስጥ ችግርዎ ከእኛ ስልጣን ውጪ ከሆነ የማረጋገጫ ደብዳቤ እንልክልዎታለን።

## ሁሉም ብቁ አመልካቾች ቅናሹን ያገኛሉ?

እንደ ሁኔታው ነው። የገንዘብ ተቋሙ የዲሲ ህጎችንና ደንቦችን መከተል የማያስፈልገው ከሆነ አንድን ችግር ለመርዳት ላንችል እንችላለን ነገር ግን ችግርዎ ከእኛ ስልጣን ውጪ ከሆነ ሌላ የመንግስት ኤጀንሲ እርዳታ እንዲያደርግልዎ ልናገናኝዎ እንችላለን።

## ማወቅ ያሉብኝ ተጨማሪ መስፈርቶች አሉ?

ህጋዊ እርምጃ ከወሰዱ እርስዎን ልንወክል አንችልም ስለዚህ ጠበቃ ማማከር ሊኖርብዎት ይችላል።

## ጥያቄዎች ቢኖሩኝ ማነጋገር ያለብኝ ማንን ነው?

መጀመሪያ፣ በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን በገጹ የታችኛው ስፍራ ላይ ይመልከቱ።
አሁንም ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎ የደንበኛ አገልግሎቶች ቡድናችንን በ (202) 727-8000 ላይ ከሰኞ እስከ አርብ ከ8:15 am to 4:45 pm ባለው ጊዜ ያግኙን። “ጥያቄ አለኝ”

በሚል ርዕሰ መስመር በ disbcomplaints@dc.gov ወደ እኛ ኢሜይል ማድረግ ይችላሉ።

**በፍጆታዎቼ ላይ አሁንም እርዳታ እፈልጋለሁ። ምን ማድረግ አለብኝ?**
በእኛየገንዘብ ሀብቶች ገጽ ላይ ሊረዱዎ ስለሚችሉ ሌሎች ሀብቶች መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

# በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## የዲሲ መንግስት የሚመረምረው ምን አይነት የገንዘብ ተቋምን ነው?

እኛ — የዲሲ መንግስት— የምንመረምራቸው የገንዘብ ተቋማት ምሳሌዎች የሚያካትቱት ባንኮች፣ የኢንሹራንስ ድርጅቶች፣ የተማሪዎች ብድር አገልግሎት አቅራቢዎች፣ የሞርጌጅ አበዳሪዎች፣ የቼክ ካሸሮች፣ የአገልግሎት ውሎች፣ የኢንቨስትመንት አማካሪዎች እንዲሁም የግምገማ ድርጅቶች ናቸው። የገንዘብ ተቋሙ የዲሲ ህጎችንና ደንቦችን መከተል የማያስፈልገው ከሆነ አንድን ችግር ለመርዳት አንችልም ነገር ግን ችግርዎ ከእኛ ስልጣን ውጪ ከሆነ ሌላ የመንግስት ኤጀንሲ እርዳታ እንዲያደርግልዎ ልናገናኝዎ እንችላለን።

## የዲሲ መንግስት ምን አይነት ጉዳዮች ላይ ምርመራ ሊያደርግ ይችላል?

ከባንክዎ፣ ከኢንሹራንስ ድርጅትዎ፣ ከአበዳሪዎ ወይም ከሌላ የገንዘብ ተቋም ጋር በሚኖሩ ማንኛውም አሳሳቢ ጉዳዮች ጋር ድጋፍ ልናደርግልዎ እንችላለን። በተጨማሪም፣ የተማሪ ብድሮችዎን እንዴት መልሰው እንደሚከፍሉ እንረዳዎታለን።

## የዲሲ መንግስት ችግር ውስጥ ካለሁበት የገንዘብ ተቋም ጋር ይነጋገራል?

ወደ እርስዎ የገንዘብ ተቋም የእርዳታ ጥያቄ ቅጂውን ልናስተላልፍ እንችላለን እንዲሁም ማብራሪያ እንዲሰጡን ልንጠይቅ እንችላለን። የዲሲ ህጎችንና ደንቦችን መተላለፋቸውን

ለማወቅ ማብራሪያቸውን እንገመግማለን። ጥሰት ካገኘን፣ ችግሩን ለማስተካከል እርምጃ እንዲወስዱ ልንጠይቃቸው እንችላለን።

## ከገንዘብ ተቋሙ ጋር ያለኝን ስምምነት የዲሲ መንግስት እንድገነዘበው ይረዳኛል?

አዎ፣ ችግሩን የሚፈታው ከሆነ ከገንዘብ ተቋሙ ጋር ያለውን የእርስዎን ስምምነት ዝርዝሮች ልናስረዳ እንችላለን።

## የገንዘብ ተቋሙ ተግባራት ማንኛውንም የዲሲ ህጎችና ደንቦች ጥሶ ካልተገኘ፣ የዲሲ መንግስት እርዳታ ለማቅረብ ምን ሊያደርግ ይችላል?

ድርጅቱ ማንኛውንም የዲሲ ህጎችና ደንቦች ጥሶ ካልተገኘ፣ ችግርዎን ለመፍታት ለእርስዎ አማራጭ መፍትሄዎችን ልንጠቁምዎ እንችላለን። ችግርዎ ከእኛ ስልጣን ውጪ ከሆነ፣ ያ ሊያጠቃልል የሚችለው ሌላ የመንግስት ኤጀንሲ እንዲያገኙ በማገዝ ነው።

## የዲሲ መንግስት በፍርድ ቤት ውስጥ እኔን ሊወክል ይችላል?

አይ፣ የእርስዎ ህጋዊ ተወካይ ልንሆን ወይም በፍርድ ቤት ውስጥ ወይም ውጪ ባለ ክስ ውስጥ ጣልቃ ልንገባ አንችልም። ምክንያቱም እርስዎን በህጋዊ እርምጃዎች ውስጥ ልንወክል ወይም ህጋዊ ምክር ልንሰጥ አንችልም፤ ጠበቃ ማማከር ሊኖርብዎት ይችላል። የሐራጅ ሽያጭ ሰጋት ወይም ሒደት ውስጥ ከሆኑ ሕጋዊ አገልግሎቶችን ወደሚያካትተው የእኛ[የሐራጅ ሽያጭ መከላከያ ፕሮግራም] ልናስተላልፍዎ እንችላለን።

## የዲሲ መንግስት የተከለከልኩትን የህክምና ኢንሹራንስ ይገባኛል ጥያቄዬን ሊመረምር ይችላል?

የኢንሹራንስ ድርጅቱ የእርስዎን የህክምና ይገባኛል ጥያቄ የከለከለው ተአማኒነት ባለው ምክንያት እንደሆነ ወይም ድርጅቱ የእርስዎን ስምምነት ወይም ማንኛውም የዲሲ ህጎች

ወይም ደንቦችን መተላለፋቸውን መመርመር እንችላለን። ነገር ግን፣ ስለእርስዎ የህክምና ሁኔታ ማንኛውም ምክር ወይም ውሳኔዎች ልንሰጥዎ አንችልም።

## የዲሲ መንግስት የገንዘብ ተቋሙ እውነቱን እየተናገረ እንደሆነ ሊያውቅ ይችላል?

አይ፣ ችግሮችዎን የከበቡትን የእውነታ ክርክሮች እልባት መስጠት ወይም በእርስዎና በገንዘብ ተቋምዎ መካከል ባለው ክርክር ላይ ማን እውነቱን እየተናገረ እንደሆነ መወሰን አንችልም።

## የዲሲ መንግስት ችግሬን መርምሮ እስኪያጠናቅቅ ድረስ የሞተር መኪናዎች ክፍል (DMV) ቅጣቴን ሊያቆይ ይችላል?

አይ፣ በምንመረምርበት ወቅት DMVን ቅጣትዎን እንዲያቆይ መጠየቅ አንችልም።

## የዲሲ መንግስት ለእኔ የሚሆን የገንዘብ ተቋም ሊጠቁመኝ ይችላል?

አይ፣ ጥቆማዎችን መስጠት ወይም የትኛው የገንዘብ ተቋም ጋር የንግድ እንቅስቃሴ ለማድረግ እንዲወስኑ እርዳታ ማድረግ አንችልም።

## የዲሲ መንግስት ከገንዘብ ተቋሙ ሚስጥራዊ ሰነዶችን ሊጋራ ይችላል?

በሚያሳዝን ሁኔታ የገንዘብ ተቋሙ ሚስጥራዊ ናቸው ያለንን ሰነዶች መጋራት አንችልም። በፍርድ ቤት የታዘዙ የሰነድ ጥያቄዎችን እናከብራለን።

## ከብዙ አመታት በፊት ጀምሮ ያልተፈታ ችግር አለኝ። ሊረዱኝ ይችላሉ?

እንደ ሁኔታው ነው። ህጉ በብቸኝነት የሚጠይቀው የገንዘብ ተቋማት የተወሰኑ መዝገቦችን እስከ 7 አመታት ድረስ እንደሚያቆዩ ነው፣ ስለዚህ ችግርዎ ከ 7 አመታት በላይ የቆየ ከሆነ እርዳታ ማድረግ ላንችል እንችላለን።

## በምርመራው ውጤቶች ካልረካሁ ምን ይፈጠራል?

በምርመራው ውጤቶች ካልረኩ፣ ልምድ ባለው አስተዳደራችን ግኝቶቹ ግምገማ እንዲደረግባቸው መጠየቅ ይችላሉ። ስራ አስኪያጁ የመርማሪውን ፋይሎች እና አሳሳቢ ጉዳዮችዎን በመገምገም ከእርስዎ ጋር ስለ ግኝቶቹ ይወያያሉ። የስራ አስኪያጁን ግምገማ ማግኘት ከፈለጉ፣ የእኛን የደንበኛ አገልግሎቶች ቡድን በ (202) 727-8000 ላይ ከሰኞ እስከ አርብ ከ8:15 am to 4:45 pm ባለው ጊዜ ያግኙ። ወይም በ disbcomplaints@dc.gov ላይ ኢሜይል ሊያደርጉልን ይችላሉ።

*ይህ ገጽ ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው ፌብሩዋሪ 2021 ነው።*